3

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፴፭
አዲስ አበባ የካቲት ፴ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

21st Year No. 35
ADDIS ABABA, 9th March, 2015

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፫፻፵፪/፪ሺ፯ ዓ.ም

የሃይማኖት ወይም የበጎ አድራጎት ድርጅቶች በቅጥር ላይ የተመሠረቱ የሥራ ግንኙነቶች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ……………………………………ገጽ ፰ሺ፩፻፵፱

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፵፪/፪ሺ፯

## የሃይማኖት ወይም የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ከሠራተኞቻቸው ጋር ስለሚመሠርቱት በቅጥር ላይ የተመሰረተ የሥራ ግንኙነት የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፫ አንቀጽ ፭ እና በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር ፫፻፸፯/፲፱፻፺፮ አንቀጽ ፫ (፫) (ለ) መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የሃይማኖት ወይም የበጎ አድራጎት ድርጅቶች በቅጥር ላይ የተመሠረቱ የሥራ ግንኙነቶች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፵፪/፪ሺ፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

፩/ "መንፈሳዊ አገልግሎት" ማለት በሃይማኖት ድርጅት ውስጥ ከእምነት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን መንፈሳዊ ተግባራትን ብቻ ማከናወን ነው፤

CONTENTS

Regulation No.342/2015

Employment Relations Established by Religious and Charitable Organizations Council of Ministers Regulation……………………………………Page 8149

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 342/2015

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION ON EMPLOYMENT RELATIONS ESTABLISHED BY RELIGIOUS AND CHARITABLE ORGANIZATIONS

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 3 (3) (b) of the Labour Proclamation No. 377/2003.

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as the "Employment Relations Established by Religious and Charitable Organizations Council of Ministers Regulation No. 342/2015".

**2. Definitions**

In this Regulation, unless the context otherwise requires:

1/ "spiritual service" means a service which is performed only to discharge functions directly related with spiritual activities in a religious organization;

፪/ "የበጎ አድራጎት ድርጅት" ማለት ትርፍ የማግኘት ዓላማ የሌለው ሰብዓዊ፣ ማኅበራዊ ወይም የልማት አገልግሎት ለሕዝብ ለማበርከት የተቋቋመ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ወይም ማኅበር ነው፤

፫/ "ገቢ ማስገኛ ሥራ" ማለት የሃይማኖት ወይም የበጎ አድራጎት ድርጅት ገቢ ለማግኘት ባቋቋመው ድርጅት ሥር የሚከናወን ዕቃዎችን የማምረት ወይም የማከፋፈል፣ አገልግሎት የመስጠት ወይም ሌላ መሰል የገቢ ማስገኛ ሥራ ነው፤

፬/ "ሚኒስቴር" ማለት የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ነው፤

፭/ "አዋጅ" ማለት የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር ፫፻፸፯/፲፱፻፺፮ ነው።

፫. <u>የሃይማኖት ድርጅቶች በቅጥር ላይ የተመሠረቱ የሥራ ግንኙነቶች</u>

፩/ በሃይማኖት ድርጅቶች ውስጥ መንፈሳዊ አገልግሎት የሚሰጡ አገልጋዮች ላይ አዋጁ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

፪/ በሃይማኖት ድርጅቶች ውስጥ መንፈሳዊና አስተዳደራዊ ወይም መንፈሳዊና የበጎ አድራጎት ተግባር በአንድ ሰው በጣምራ ከተከናወነ አዋጁ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

፫/ በሃይማኖት ድርጅቶች ውስጥ በገቢ ማስገኛ ሥራዎች ላይ በተሠማሩ ሠራተኞች ላይ አዋጁ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

፬/ በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፭ ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በሃይማኖት ድርጅቶች ውስጥ አስተዳደራዊ ወይም የበጎ አድራጎት ተግባርን ለማከናወን በተሰማሩ ሠራተኞች ላይ አዋጁ ተፈፃሚነት ይኖረዋል።



2/ "charitable organization" means a non-governmental organization or society established for non-profit making purposes but provides humanitarian, societal or developmental services;

3/ "income generating activity'' means the production or distribution of goods, the provision of services or other similar income generating activity performed by enterprises established under a religious or charitable organization;

4/ "Ministry'' means the Ministry of Labour and Social Affairs;

5/ "Proclamation" means the Labour Proclamation No. 377/2003.

3. **<u>Employment Relations Established by Religious Organizations</u>**

1/ The Proclamation shall not be applicable with respect to a person who gives spiritual service in a religious organization.

2/ The Proclamation shall not be applicable with respect to a person who performs spiritual and administrative or spiritual and charitable activities, simultaneously, in a religious organization.

3/ The Proclamation shall be applicable with respect to workers engaged in performing income generating activities undertaken by religious organizations.

4/ Without prejudice to Article 5 of this Regulation, the Proclamation shall be applicable with respect to workers engaged in performing administrative or charity activities in religious organizations.

፬. <u>የበጎ አድራጎት ድርጅት በቅጥር ላይ የተመሠረቱ የሥራ ግንኙነቶች</u>

፩/ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ገቢ ለማግኘት በሚያቋቁሟቸው ድርጅቶች ውስጥ የገቢ ማስገኛ ሥራዎች ላይ በተሠማሩ ሠራተኞች ላይ አዋጁ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

፪/ በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፭ ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በበጎ አድራጎት ድርጅቶች ውስጥ አስተዳደራዊ ወይም የበጎ አድራጎት ተግባርን ለማከናወን በተሠማሩ ሠራተኞች ላይ አዋጁ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

፭. <u>የኅብረት ድርድር</u>

፩/ የሃይማኖት ወይም የበጎ አድራጎት ድርጅቶች በአስተዳደራዊ ወይም በበጎ አድራጎት ሥራ ላይ ከተሠማሩ ሠራተኛ ጋር የደመወዝ ጭማሪ፣ ልዩ ልዩ ጥቅሞች፣ ማበረታቻዎችና የመሳሰሉትን በሚመለከት የኅብረት ድርድር ለማድረግ አይገደዱም፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም የደመወዝ ጭማሪ፣ ልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅሞች፣ ማበረታቻዎችና የመሳሰሉት በሃይማኖት ወይም በበጎ አድራጎት ድርጅቶች የሥራ ደንቦች ወይም የሥራ ውሎች ሊወሰኑ ይችላሉ፡፡

፮. <u>*መመሪያ የማውጣት ሥልጣን*</u>

ሚኒስቴሩ ይህን ደንብ በሚገባ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

፯. <u>ደንቡ ስለሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት ፴ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

4. <u>**Employment Relations Established by Charitable Organizations**</u>

1/ The Proclamation shall be applicable with respect to workers engaged in performing income generating activities under business enterprises established by charitable organizations.

2/ Without prejudice to Article 5 of this Regulation, the Proclamation shall be applicable with respect to workers engaged in performing administrative or charity activities in a charitable organization.

5. <u>**Collective Bargaining**</u>

1/ Religious or charitable organizations shall not be obliged to engage in collective bargaining on increment of wages, benefits, incentives and other similar matters with workers engaged in performing administrative or charity activities.

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, increment of wages, benefits, incentives and other similar matters may be governed by work rules or employment contracts of religious or charitable organizations.

6. <u>**Power to Issue Directives**</u>

The Ministry may issue directives necessary for the proper implementation of this Regulation.

7. <u>**Effective Date**</u>

This Regulation shall come into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 9th day of March, 2015.**

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

**፬. የበጎ አድራጎት ድርጅቶች በቅጥር ላይ የተመሠረቱ የሥራ ግንኙነቶች**

፩/ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ገቢ ለማግኘት በሚያቋቁሟቸው የንግድ ድርጅቶች ውስጥ የገቢ ማስገኛ ሥራዎች ላይ በተሠማሩ ሠራተኞች ላይ አዋጁ ተፈፃሚ ይሆናል።

፪/ በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፭ ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በበጎ አድራጎት ድርጅቶች ውስጥ አስተዳደራዊ ወይም የበጎ አድራጎት ተግባርን ለማከናወን በተሠማሩ ሠራተኞች ላይ አዋጁ ተፈፃሚ ይሆናል።

**፭. የኅብረት ድርድር**

፩/ የሃይማኖት ወይም የበጎ አድራጎት ድርጅቶች በአስተዳደራዊ ወይም በበጎ አድራጎት ሥራ ላይ ከተሠማሩ ሠራተኞች ጋር የደመወዝ ጭማሪ፣ ልዩ ልዩ ጥቅማጥቅሞች፣ ማበረታቻዎችንና ተመሳሳይ ጉዳዮችን በተመለከተ የኅብረት ድርድር ለማድረግ አይገደዱም።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም የደመወዝ ጭማሪ፣ ልዩ ልዩ ጥቅሞች፣ ጥቅማጥቅሞች፣ ማበረታቻዎችና የመሳሰሉት ጉዳዮች በሃይማኖት ወይም በበጎ አድራጎት ድርጅቶች የሥራ ደንብ ወይም የሥራ ውል ሊወሰኑ ይችላሉ።

**፮. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

ሚኒስቴሩ ይህን ደንብ በሚገባ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

**፯. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ የካቲት ፴ ቀን ፳፻፯ ዓ.ም

ኃይለማርያም ደሣለኝ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

**4. Employment Relations Established by Charitable Organizations**

1/ The Proclamation shall be applicable with respect to workers engaged in performing income generating activities under business enterprises established by charitable organizations.

2/ Without prejudice to Article 5 of this Regulation, the Proclamation shall be applicable with respect to workers engaged in performing administrative or charity activities in a charitable organization.

**5. Collective Bargaining**

1/ Religious or charitable organizations shall not be obliged to engage in collective bargaining on increment of wages, benefits, incentives and other similar matters with workers engaged in performing administrative or charity activities.

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, increment of wages, benefits, incentives and other similar matters may be governed by work rules or employment contracts of religious or charitable organizations.

**6. Power to Issue Directives**

The Ministry may issue directives necessary for the proper implementation of this Regulation.

**7. Effective Date**

This Regulation shall come into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, this 9th day of March, 2015.

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

**ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ**